# ብዕር ፣ ነው ጠላቱ

የስም ፣ ሰላም ወዳድ ፣ ዜጋን አስታራቂ
የሚሳነው የለ ፣ ሁሉንም አዋቂ
ያከበረውን ህዝብ ፣ አጣጥሎ ናቂ
ቃላት በማሳመር ፣ ወሬውን ጠራቂ
    የኦነግ አላማን ፣ ያነገበ አስጠቂ
    ተምኔታዊ ሀገር ፣ ቅዠትን ናፋቂ ።

የበሸሻ አብዮት ፣ የሸገር አብዩ
አውድሱኝ እንጂ ፣ አትተቹኝ ባዩ
እራሱን የሚያየው ፣ ከሰው ፣ አርጎ ልዩ
ኢትዮጵያን እያለ ፣ ሰባኪ አስመሳዩ
    የለበሰው ጭምብል ፣ ተገፎ ከላዩ
    ሲደነፋ አመሸ ፣ ሲል ፣ ቡራ ከረዩ ።

እራሱን ሳይገራ ፣ አገርን ሊመራ
ከንዱን አፈርጥሞ ፣ በቄሮ ገጀራ
የሱ ፣ ስውር ቅኔ ፣ ለኛ ተሰውራ
ሱሉልታ ቡራዩ ፣ ብሎ እየተጣራ
እሳት የሚሊኩስ ፣ የሚያስነሳ አቧራ
ሰላምን ሳይፈጥር ፣ ከህሊናው ጋራ
    መድረክ እየወጣ ፣ በከንቱ ፉከራ
    በፍርሃት ዛቻ ፣ ይታያል ሲያቅራራ ።

ሞግተህ አሸንፍ ፣ የሚለው አንበሳው
ምነው ዛሬ ፣ በሃሳብ ፣ ኮስሶ የከሳው
ብስጭትጭት ማለቱን ፣ አሁን ፣ ምን አስነሳው
ሲተች የማንሰማው ፣ ገጀራ ላነሳው
    በስከንድር ላይ ፣ ሆነ ፣ ቁጭቱ ወቀሳው
    ሰላማዊው ትግል ፣ ለምን ፣ እረፍት ነሳው ።

ለሃምሳ ዓመት ፣ ሙሉ ፣ ጥላቻ ተዘርቶ
ያንን ሲያቀነቅን ፣ ያደገው ተግቶ
ጥርስ የነቀለበት ፣ እምነቱን አንግቶ
ኢትዮጵያ እያለ ፣ በደረቁ ላጭቶ
ምኞቱን ሊያሳካ ፣ ህዝብን አዘናግቶ
ነበረ ዓላማው ፣ ስር ፣ ቢሰድ ቆይቶ
    ትላንት መሰከረ ፣ ሳያስበው ስቶ
    ሰበታ ሱሉልታ ፣ አለን ፣ አፉን ሞልቶ ።

የጣውላዎች ክምር ፣ ሚስማር የተመቱ
ገጀራና አጣና ፣ ቢቆሙ ከፊቱ
አመድ የሚመስለው ፣ ተለውጦ ፊቱ
ከወሰን የሚያልፈው ፣ ንዴት ፣ ደም ፍላቱ
የሚይዘው ጠፍቶት ፣ እንዲህ መርበትበቱ
    እስከንድር የያዘው ፣ እርሳስ ወረቀቱ
    እሱን የሚያስፈራው ፣ ብዕር ፣ ነው ጠላቱ ።

ታዛቢው

March 25, 2019